ካማህተመ ፍቅረስላሴ
Fikre100@gmail.com

# የለውጡ መሰረቱ ሕገ መንግስት ወይስ ጠቂቶችን ለማስደሰት ?

ሀገሪቱ ላይ እየመጣ ያለው ሁለተናዊ መረጋጋት በተለይም የማህበረሰብን ፖለቲካ ከማረጋጋት ጋር በተያያዘ እምርታው አጥጋቢ እና አስደሳች እየሆነ ይገኛል፡፡ይህም አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር ሚናቸው በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

እርግጥ ነው አንድ አንዱ ውሳኒያቸው ፕሬዚዲንሻል ሲስተም ከሚጠቀሙ አገሮች ጋር ተመሳሳይ የሚያደርጋቸው ነገሮች እየወሰዱ ይገኛሉ፡፡ለዚህ ማሳያ የሀገሪቱ መሪ የስልጣን ዘመን ሁለት የምርጫ ዘመን ለማድረግ እሰራለሁ ማለታቸው ነው፡፡

የመሪውን ስልጣን መገደብ ከለው አገራዊ ፋይዳ አንፃር ከፍተኛ ሲሆን ይህም አንድ መሪ እንደፈለገው አድራጊ ሰባሪ እንዳያደርገው ወይም ካደረገውም የስልጣን ገደብ በመኖሩ ቀጣይነት እንዳይኖሮው ያደርገዋል፡፡

ሌላው ካቢኖዎች እና ሚኒስተር ዲኤታዎች እንዲሁም ዳይሬክቶሮች የሚሸሙበት አግባብ ቀድሞ ከነበረው የሚለይ ይመስለኛል፡፡ለዚህ ማሳያ በትግራይ ተወላጆች ስር ይመሩ የነበሩ ቦታዎች መቀነሳቸው ነው፡፡

ሌላው ከአሜሪካ የከፍተኛ አመራሮች አፀዳደቅ የተወሰደ በሚመስል የሀገራችን ጠቅላይ ሚኒስተር ካቢኖቻቸው በፓርላማ በዘርፉ ቋሚ ኮሚቴ ጋር የስራ ውል እንዲያስሩ ይደረጋል ማለታቸው ነው፡፡

እንዲሁም ከዚህ ቀደም የነበሩ መሪዎች የንግግራቸው መጀመሪያ እና መጨረሻ ፓርቲያቸውን ያጠነጠነ ሲሆን የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስተር ግን ፓርቲያቸውን የዘነገ ይመስላል፡፡

እናም አንድ አንድ ጓደኞች ሀገራችን ከልማታዊ መንግስት ወደ ኒው ሊበራል ሲስተም ለመቀየር የተጀመሩ መንገዶች ናቸው ይሉኛል፡፡

እርግጥ ነው እላይ የተጠቀሱት በሙሉ በአብዛህኛው መልካም ነገሮች ናቸው ፣ ግን ሲስተም ለውጥ እያደረግን መሆናችን እና አለመሆናችን ጠቅላይ ሚኒስተሩ ማረጋገጫ ቢሰጡን ጥሩ ነገር ይመስለኛል፡፡

ከዚህ ጋር በተያይዙ ሀገራችን እየመራት የሚገኘው ጠቅላይ ሚኒስተሩ ነው ወይስ ፓርቲው ነው ያስብላል፡፡

እውነት ግን ሀገራችን እየመራት የሚገኘው ጠቅላይ ሚኒስተሩ ነው ወይስ ፓርቲው ?

እንደው ለመጠየቅ ያክል ነው እንጂ ፓርቲው መራው ጠቅላይ ሚኒስተሩ ብቻ አብዛህኛውን ህዝብ መሰረት ያደረገ ፣ የሚያስደስት እና ያገናዘበ ስራ ይሰራ ነው ቁምነገሩ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስተሩ እየለወጧቸው ከሚገኙ ነገሮች አንዱ የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ መሰረት ያደረገ ስራዎች መስራት እንደሆነ በተለያዩ መድረኮች አንስተውታል፡፡ከዚህም ጋር በተያያዘ የወርቅ ተሸላሚዎች ልዩ ትኩረት እንደሚሰጣቸው እና ይህንን ለማስፈፀም አዲስ ፕሮጀክት እንደተጀመረ ገልፀውሉናል፡፡

ይህ በጣም የሚያበረታታ ነገር ሲሆን ከምንም በላይ ግን ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ሌላው ተመራቂ ተማሪ ላይ ስራ ዕድል ከመፍጠር አንፃር ላይ መሆን አለበት፡፡በአብዛህኛው ከፍተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ ተማሪዎች በስራ ላይ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘግባሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ብዙ ግዜ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲዎች ገብተው ሌላን

ካማህተመ ፍቅረስላሴ
Fikre100@gmail.com

ተተኪ ያበቃሉ ብለን ስንጠብቅ በእነ ግሙሩክ እና መሰል ተቋማት ገብተው ዕቃ በመፈተሸ ግዚያቸውን ዕድሚያቸውን እና እውቀታቸውን ያሳልፋሉ፡፡

መማር በእርግጥ ያስተሳሰብ አድማስን የማስፋት አቅም ያለው ቢሆንም እነዚህ ኀበዝ የተባሉ ዜጎች ከተመረቁ በኋላ ነጥብ ተጠይቀው ትልልቅ መስሪያ ቤቶች ከገቡ በኋላ በቀላል ስልጠና የሚሰሩ ስራዎች ላይ ተቀምጠው ፣ ተመደበው ሲሰሩ ይታያሉ፡፡

ምሳሌ ለመጥቀስ ያክል ገቢዎች ፣ ባንኮች ፣ አንድ አንድ የልማት ድርጅቶች ከፍተኛ ነጥብ ያላቸውን በመቅጠር የሚያሰማራቸው ግን ያን ያህል የልጆቹን ዕውቀት እና ብቃት ሊጠቀሙበት ወይም ሊመራመሩበት የሚችል ቦታ አይደለም፡፡

ከዚህ አይነት የቅጥር ስርዓት ወደ ሌላኛው የቅጥር ስርዓት ብንገባ የተሻለ ነው፡፡

እንዴት ከላችሁ ሁሉም ሰው ተወዳድሮ እና ተፈትኖ ስራ ማግኘት አለበት ፣ ድርጅቶች ውጤት ተኮር የሆነ ቅጥር ከማስኬድ ሜሪት መሰረት ያደረገ የቅጥር ስረዓት መከተል አለባቸው፡፡

እርግጥ ነው ውጤት የሚጠይቁ የስራ ዘርፎች አሉ፡፡ምሳሌ የትምህረት ማዕከላት ፣ የምርምር ማዕከላት ፣ የዲዛይን ስራ ወዘተ ውጤትን መሰረት ያደረገ ቢሆን ሲኬታማ ሰራተኛ ማግኘት ይቻላል፡፡

አብዛህኛው የአለም ባንክ ድርጅቶች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቅጥር ሂደታቸው ሜሪት ቤዝ በመሆኑ ለስራው በዕውቀት + በክህሎት ብቁ የሆነ ስራተኞች ይወስዳሉ፡፡

በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ሲወሰን የቅጥር ሁኔታ እና የስራ ዕድል ፈጠራ አብሮ መታሰብ አለበት፡፡እኔ አንድ አንድ ጊዜ ግራ የሚገባኝ የግል ድርጅቶችስ ጥሩ የግል ነው፤ የመንግስት ድረጅቶች ግን ዩኒቨርሲቲ ላስመረቀው ተማሪ አንተ ብቁ አይደለህም ብሎ በነጥብስ መቅጠር እና መከልከል መብት አላቸው ? በበኩሉ ሁሉም ዜጋ እኩል ተጠቃሚ መሆን ስላለባቸው ቀጣሪዎች እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ ሊያዘጋጁ ይገባል፡፡

አሁን አሁን ደግሞ በቅርብ አመታት እያጋጠመ ያለው ከፍተኛ ችግር በተፈጥሮ ሳይንስ የሚመረቁ ተማሪዎች የስራ ዕድል ማጣት እና መበራከታቸው ነው፡፡የእውነት በጣም ያሳዝናሉ ፣ አምስት አመት ተምረው ፣ ለፍተው ተመርቀው ማንም ሳይቀጥራቸው አመታት በቤት ማሳለፋቸው እነሱ ላይ ከሚነሳው የሞራል ውድቀት በዘለለ ሀገር ላይ የሚያደርሰው በተለይም በማህበራዊ ሆነ በኢኮኖሚያዊ ረገድ ከፍተኛ ጉዳት ነው፡፡

የአንድ አንድ አመራሮች መልስ ሀግሪቱ ተገንብታ ያልተጠናቀቀች በመሆኖ የተፈጥሮ ዘርፍ ከፍተኛ የስራ ዕድል ይፈጠርለታል በሚል ታሳቢ ነው፡፡ያው ስራ ዕድል ፈጠራ ሲባል ማደራጀት ይነሳል፡፡

የተመረቁ ተማሪዎች በተጨባጭ አደራጅቶ ትንንሽ ስራዎች ለማሰራት የሚፈጀው ጊዜ ከአንድ አመት እስከ ሁለት አመት ይፈልጋል ወይ ይፈጃሉ፡፡ከተደራጁም በኋላ ብድር ለማግኘት እንዲሁ ወራት አመታትም ሊፈጅ ይችላል፡፡ብድሩም ቢሆን ተያዥ አምጣ በሚል ሰበብ አብዛሀኛው የፋይናንስ ተቋማት ሌላ ችግር ይፈጥራሉ፡፡

ካማህተመ ፍቅረስላሴ
Fikre100@gmail.com

በስንት መከራ የተደራጀው ደግሞ በሙሰኞች ስራቸው ልፋታቸው ከንቱ ይደርሳል፡፡

ይህ ነው እውነታው ፤ ስለዚህ መንግስት የትምህርት ፖሊሲውን የተፈጥሮ ሳይንስ ተኮር ስትራቴጂ ውጤት እና ፈተናውን በመገምገም ሊያሻሽለው ይገባል፡፡

ምክንያቱም ስራ የፈታ ወጣት ያለው አማራጭ አንድም ሀገሩን ሸሽቶ መሄድ ነው ፣ ሌላው ገንዘብ ሊያገኝ የሚችልበት ቀዳዳ መፈለግ ብሎም ራሱን የሚረሳበት ፣የሚደበቅበት ሁኔታዎች መፈለግ ነው፡፡

ሌላው አዲሱ አመራር እያሳየ ካለው ነገር መካከል ግንባር ቀደሙ የእስረኞች መፈታት ነው፡፡

እስረኞች ምህረት መስጠት የሚሰጠው መልካም ነገር እንዳለ ሁኖ የሚያስከትለው አሉታዊ ነገር ግን እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

ህጎች በማንኛውም ሁኔታ ጥንካሪያቸው ሊያጡ አይገባም፡፡

ጠንካራ ህግ መኖር የመንግስትን እና የህዝብን ግንኙነት ፣ ስራ፣እና ሙብት እና ግዴታ በሚገባ ይለያል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ አሁን እሆን ያለው ነገር ወደ ፊት ዜጎች በሀገራችው ህግ ላይ እምነት እንዳይኖራቸው ሊያደረግ ይችላል፡፡ምክንያቱም ምህረት የሚሰጠው አካል እና ክስ የሚቋረጥለት ግለሰቦች የተያዙበት ሁኔታ ከፍተኛ ችግር ያስከተለ እና የሚያስከትል ስለነበር ነው፡፡

ክስ ከተቋረጠላቸው ግለሰቦች ድርጅቶች መካከል ሀገሪቱን በጦርነት ለማተራመስ አልመው፣ አስበው፣ አቅደው የተነሱ እንደነበሩበት በተለያዩ መገናኛ ሚድያዎች ስንስማ ነበር፡፡እንዲሁም በከፍተኛ ሙስና ወንጀል ተጠርጥረው የገቡ ግለሰቦችም ነበሩ፡፡

በግሌ ምህረት መስጠት የፍቅር መገለጫ ሲሆን ቁምነገሩ ግን ሁሉም ምህረት የሚሰጣቸው ዜጎች እና ክሳቸው የተቋረጠ ድርጅቶች ሆኑ ሰዎች ላይ በትንሹም ቢሆን መግባባት እና መተማመን ተደርሶ መሆን አለበት፡፡

አንዳ አንዶቹ የተፈቱ ግለሰቦች ከተፈቱ በኋላ የሚሰጡት አስተያየት ከነበሩበት አመለካከት ያለመለወጣቸው የሚያሳይ ነው፡፡ይህም አንድም ተመሳሳይ ስራ ሲሰሩ ከተያዙ መንግስት ላይ የሚሰጠው ስያሜ ማለትም ፈቶ አሰራቸው ከጅምሩም የህዝብን አቅጣጫ ለማስቀየር ነበር እንጂ ከልብ የተደረገ ነገር አይደለም የሚያስብል ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ ያንን ላለመባል ዝም ይባላሉ ማለት ነው፡፡ይህ በሂደት የሀገሪቱ ህግ ላይ እምነት እንዳይጣል ያደረጋል፡፡ እንደሚታወቀው አንድ አንድ ድርጅቶች መንግስትን ለማውረድ ብቸኛ መንገድ በጦር ሃይል ነው በሚል ተደራጅተው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡እነዚህ ድርጅቶች የሀገሪቱን ህገ መንግስት አንቀበልም ብለው በይፋ ወደ ጦርነት አውደ መዳ የገቡ ናቸው፡፡አላማቸውን ለማሳካት ሲንቀሳቀሱ የተያዙ ድርጅቶቹ አባላት ለአመታት እስር ቤት እንደነበሩ ይታወቃል፡፡

በግሌ ምህረት የሚሰጠው አካል ማን ምን ያደረገ ነው የሚለው ነገር በጥልቅ ተመርምሮ በህግ የተደገፈ መሆን አለበት ፡፡ምክንያቱም የግለሰብ ወይም የመሪዎች ወይም የፓርቲ ይሁንታ ላይ የተመሰረተ ምህረት ፣ ክስ ማቋረጥ ከሆነ አሁንም የህግ የበላይነት ትርጉሙ እና ድርጊቱ ያጣል ፣ የስራ አስፈፃሚው የበላይነት ይጨምራል ማለት ነው፡፡

ካማህተመ ፍቅረስላሴ
Fikre100@gmail.com

በመሆኑም ክስ የሚቋረጥለት ግለ ሰብ ወይም ድርጅት እንዲሁም ምህረት የሚገኙ በአጠቃላይ የህግ ማዕቀፍ ያስፈልጋል፡፡

አሁን እየሆነ ያለው ህግ ማዕቀፍ መሰረት ተደርጎ እየተሰራ የሚመስል ነገር ማስታዋል ስላልቻልኩ ነው፡፡ምክንያቱም ለምሳሌ ግንቦት 7 መወሰድ እንችላለን፡፡

አሜሪካ ከአሸባሪዎች ጋር አንደራደርም የሚል አቋም ስላላት ማንኛውም ግንኙነት ከብሔራዊ ደህንነት ጋር በማያያዝ አሸባሪ ብላ የፈረጀችውን አካል ለማጥፋት ፣ ለመደምሰስ ትንቀሰቀሳለች፡፡በዚህ ማህል የወታደሮቻ ሂይወት ማጣት ጨምሮ ብዙ ገንዘብ ፈሰስ ታደርጋለች፡፡

በዚህ ሁኔታ የተያዘ ፣ የተማረከ የአሸባሪ አባል የሚገባውን ቅጣት ትሰጣለች፡፡

ግንቦት ሰባት መንግስት አሸባሪ ብሎ ፈረጀ አልፈረጀ ድርጅቱ በራሱ የሚከተለው ፖሊሲ እና ስትራቴጂ አጥፊ አውዳሚ ነው፤በራሱም በመሪዎቹም በግልፅ አስቀመጠውታል፡፡

በድርጅቱ አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ በቀጥታ የደረሰ ውድመት ለመግለፅ ባዳግተኝም  የድርጅቱ አባላት ግን በመንግስት ቁጥጥር ስር ሲውሉ ምህረት እንዲደረግላቸው ካስፈለገ ወይ የተያዘው ሰው አመለካከት እና የትግል መንገድ ከምንግስት ጋር ተማምኖ መረዳዳት ላይ ሲደረስ ነው አልያም ከዋናው ድርጅት ጋር መንግስት ተደራድሮ መስማማት ላይ ሲደርስ ብቻ መሆን አለበት፡፡እየሆነ ያለው ግን እንደዚህ አይደለም፡፡

ያውም ሰዎች ባልተፈለገ መንገድ ብንሰማራ እና የተወሰኑ ሰዎች አገሮች ቢደግፉን ብንታሰርም መለቀቃችን አይቀርም በሚል ሰበብ ወደ አልተፈለገ እንቅስቃሴ እንዲገቡ በር ይከፍታል፡፡

እንደ ቻይና እና ጃፓን የመሳሰሉ አገሮች ሙስናን እና ሌብነትን ለመከላከል የሚያወጡት ህግ በጣም ጠንካራ እና አስፈሪ ነው፡፡አንድ አንድ የበለፀጉ አገሮች ደግሞ እነዚህን ለመዋጋት ከመሰረቱ የሰሩት ስራ አመለካከት ክፍተኛ ውጤት በማስመስገቡ ህግ እንኳን ባይኖር ሂሊናቸው ስለማይፈቅድ ወደ አላስፈላጊ ስራ የመግባት መንገዳቸው በጣም ጠቦ እናያለን፡፡

አንድ አንድ የአፍሪካ አገራት ደግሞ በማስተማሪም የተሰራ ስራ ባለመኖሩ እና የአስፈፃሚው የበላይነት በመግነኑ ማንኛውም ነገር በሃይል ለመስራት ይሞክራሉ፡፡

ሀገራችን ደግሞ የተነሳውን የህዝብ ተቃውሞ ለማረጋጋት የህግን የበላይነት ወደ ጎን በተወ ሁኔታ በሚመስል መልክ የአስፈፃሚው ይሁንታ እየተገኘ እስረኞች ይለቀቃሉ፡፡

ጠንካራ  ወይ በአመለካከት ህዝብን የቀየሩ አገሮች ፣ ህግን የጣሱ አካላት የሚገባቸውን ቅጣት ለመስጠጥ መጀመሪያ በህዝብ የሁንታ የፀደቀውን ህግ ህጉ ራሱ እንዲያከብረው ጠንክረው ይሰራሉ፡፡

በአጠቃላይ ህግ የሁሉም የበላይ መሆን እንዳለበት እና የበላይነቱን ራሱ ህጉ ማስመስከር እለበት ፡፡ይህን ለማድረግ ደግሞ በተለይ ህግ ባለሞያዎች በሚገባ ሊደራጁ እና ለሚሰሩበት ስራ ሊቆሙለት ፣ ሊጋፈጡለት ይገባል፡፡

ካማህተመ ፍቅረስላሴ
Fikre100@gmail.com

በአጠቃላይ መንግስት ሆነ መሪው ፓርቲ ህግን ማክበር እና ማስከበረ በተመለከተ የማይወላወል አቋም በመያዝ ፣ ህጎች ላይ ያሉ ክፍተቶች በመዝጋት ፣ የስራ አስፈፃሚ ይሁንታ ሳያስፈልግ በራሱ በህጉ ይሁንታ ብቻ ሰዎች ፣ ድርጅቶች ከሳቸው ሊቋረጥ መቻል አለባቸው ወይም ምህረት መሰጠት አለበት፡፡

ተቃውሞ በተነሳ ቁጥር የእውነት አጥፍተው የተያዙ በቁጥጥር ስር የዋሉ የጥፋተኛ ፍርድ የተሰጣው ሰዎቸ ፣ድርጅቶች እየፈታን የምንሄድ ከሆነ መጀመሪያውም ላይ የተፈቱት ሀሳባቸው ላይ መረዳዳት ባለመደረሱ ሲወጡም ወደ አጥፊነታቸው መመለሳቸው አይቀርም ፡፡ አጥፊነት ሲበረታ ደግሞ መንግስት ህጉን ለማስከበር እጁ ይረዝማል፡፡በማህል ሰው ይጎዳል፡፡መጀመሪያውም ሲታሰሩ የሆኑ ሰዎች ባለመደገፋቸው ምህረት ተስጥታቸው ሲለቀቁ ደጋፊዎቻቸው አሸናፊነት ሲሜት ሲሰማቸው ፣ እንደገና ምህረት የተሰጣቸው ዜጎች ህጉን ሲጥሱ እና በቁጥጥር ስር ሲውሉ የመንገሰት አሜኔታ ይጠፋል ተቃውሞም ይበዛል፡፡ያኔ መንግስት ወደ ማይመለስበት ችግር ይገባል፡፡

ስለዚህ ህግ ላይ ያለን አቋም ፣ ምህረት የሚያሰጡ ጉዳዮች ፣ የምህረት ሰጪው ስልጣን በአጠቃላይ በህግ ሊደገፍ እና ሊታሰር ይገባል፡፡

እናም አሁን እሆነ ያለው ነገር ወደ ፊት አገራችን ከፍተኛ ዋጋ እንዳያስከፍላት በጥንቃቄ መሆን አለበት፡፡

በአጠቃላይ ጠቅላይ ሚኒስተሩ የሚያደርጓቸው ለውጦች መሰረቱ ህገ መንግስት ያደረገ እና ጠቂቶችን ለማስደሰት አብዛህኛውን ዜጋ እንዳናጣ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡